County of Fairfax, Virginia

# ርዕስ 4 የዘር መድልዎን የተመለከተ መረጃ እና የክስ አቀራረብ መመሪያ

የ1964ቱ የሲቪል መብቶች ሕግ ርዕስ 4 አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን በማወቅም  ሆነ ባለማወቅ በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ብሔራዊ ማንነት መነሻነት በፌርፋክስ ኮኔክተር (Fairfax Connector) እና ፌርፋክስ ካውንቲ የትራንስፖርት ዲፓርትመንት (Fairfax County Department of Transportation) የትራንዚት ክንውኖችንና እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ በማናቸውም የፌዴራል ድጋፍ የሚያገኝ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ላይ መድልዎ ማድረግን ይከለክላል።

ማናቸውም በፌርፋክስ ኮኔክተር ወይም በፌርፋክስ ካንውንቲ የትራንስፖርት ዲፓርትመንት በዘሩ/ዋ፣ በቀለሙ/ሟ፣ በብሔራዊ የቀድሞ ማንነቱ/ቷ የተነሳ መድልዎ ተፈጽሞብኛል ብሎ/ላ የሚያስብ/የምታስብ ሰው በፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ፕሮግራም ቢሮ (Office of Human Rights and Equity Programs (OHREP)) ድር ጣቢያ ላይ የሚከተለውን ዩ.አር.ኤል ተጠቅሞ/ማ የሚያገኘውን/የምታገኘውን «የፌርፋክስ ኮኔክተር» የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽን በመሙላት እና በማስገባት የርዕስ 4 ክስ መመስረት ይችላል/ትችላለች፡-

http://www.fairfaxcounty.gov/ohrep/epd/

የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጹ በተጨማሪ በሚከተለው አድራሻ ተጠቅሞ በመጻፍ፡- Office of Human Rights and Equity Programs, Equity Programs Division, 12000 Government Center Parkway, Fairfax, Virginia 22035 ወይም በስልክ ቁጥር 703-324-2953, TTY 711 በመደወል ወይም ፋክስ በፋክስ ቁጥር፡- 703-324-3570 በመላክ ማግኘት ይቻላል።

ፌርፋክስ ካውንቲ የተባለው በደል በደረሰ ከ180 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የቀረቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ይመረምራል። ፌርፋክስ ካውንቲ ምርመራውን እንዲጀምር በቂ መረጃ የሚሰጡ አቤቱታዎችን ብቻ ተቀብሎ ማስተናገድ ይችላል።

አቤቱታ በደረሰው በ48 ሰዓታት ውስጥ፣ የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ፕሮግራም ቢሮ ሠራተኛ አቤቱታ አቅራቢውን አግኝቶ በማነጋገር ደረሰ ስለተባለው የመድልዎ በደል(ሎች) ከግለሰቡ አስፈላጊውን ሁሉ መረጃ በመቀበል መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ይሞላል።  አቤቱታ አቅራቢው/ዋ በዚህ መረጃ የመሰብሰብ ሂደት ላይ ትብብር እንዲያደርግ/እንድታደርግ ይጠየቃል/ትጠየቃለች። መረጃ መሰብሰቢያ ቅጹ በተሞላ በ48 ሰዓታት ውስጥ፣ የOHREP ሥራ ባልደረባ መረጃውን በመጠቀም ጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ ሕጋዊ ምርመራ እንደሚያስፈልገው ወይም ግልጽ የሆነ የመድልዎ ክስ ሊያስመሰርት የሚችል ጉዳይ መሆኑን ይወስናል።

OHREP የመጀመሪያ ደረጃ ሕጋዊ ምርመራ የሚያስፈልገው ጉዳይ እንዳለ ከወሰነ፣ ምርመራ እንዲጀመር ይደረጋል። ምርመራው፣ በደል በደረሰበት ቦታ የሚደረግ ጉብኝት፣ ከምስክሮች ጋር የሚደረግ ቃለመጠይቅ እና የሰነዶች ማሰበሰብን የሚያካትት ሲሆን በዚህ ብቻ ግን ላይገደብ ይችላል። በክሱ ላይ የተጠቀሰው/ሱት ተከሳሹ ወገን(ኖች) ቃለ መጠይቅ የሚደረግላቸው ሲሆን የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ እና ለምርመራው ተዛማጅነት ያለው መረጃ እንዲሰጡ ዕድል ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም፣ እንደ አስፈላጊነቱ ምስክሮች ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል። አንድ ጊዜ ምርመራ ከተጀመረ በኋላ ሁሉም የሚሰበሰበው መረጃ በምስጢር ይያዛል። ምርመራው በተጀመረ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ሁሉም ለምርመራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች ተጠናቀው መሟላት አለባቸው። ሰነዶቹን ለማሰባሰብ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ምርመራውን የያዘው ሠራተኛ ከOHREP አመራር የጊዜ ማረዘሚያ እንዲሰጠው ፈቃድ ይጠይቃል።

ምርመራው እንደተጠናቀቀ ሪፖርት የሚዘጋጅ ሲሆን የOHREP ሠራተኛው የውሳኔ ሃሳቡን ለOHREP ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል። የOHREP ዋና ዳይሬክተር የምርመራ ፋይሉን በማየት የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል። OHREP ለአቤቱታ አቅራቢው/ዋ የተባለው በደል በእርግጥ በማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን ያሳውቃል። ምርመራው ሲጠናቀቅ እና በአቤቱታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የተደረሱበትን ውጤት እንዲያውቁት ከተደረጉ በኋላ፣ ፋይሉ እንዲዘጋ ይደረጋል። ሁሉም ሰነዶች፣ ኦዲዮ ቴፕ ክሮችን ጨምሮ (ተገቢነት ካለው) በአቤቱታ ፋይሉ ውስጥ ይቀመጣሉ።

OHREP የመጀመሪያ ደረጃ ሕጋዊ ምርመራ የማያስፈገው ጉዳይ ነው ብሎ ከወሰነ፣ ምንም ምርመራ አይደረግም። ሆኖም ግን፣ በጉዳዩ ላይ የነበሩ የOHREP ግኝቶች በሪፖርቱ ላይ በሰነድ መልክ ይቀመጣሉ። የOHREP ግኝቶች በእኩልነት ፕሮግራም ዲቪዝዮን መመሪያ ስር የሚቀመጡ ስለሆነ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም።

ሊሆን የሚችል ጉዳይ እንዳለ ከታመነበት ወይም በአንድ ሠራተኛ ከስነምግባር ውጪ መሆን እንዳለ ከተደረሰበት፣ OHREP መወሰድ ስላለበት የዲስፕሊን እርምጃ ከፌርፋክስ ካውንቲ የሰው ሃይል ዲፓርትመንት ጋር እንዲመክርበት ለFCDOT ትዕዛዝ ይሰጣል። በምርመራ ሂደቱ ወቅት፣ መርማሪው የወንጀል ተግባር ወይም የሕግ ጥሰት እንዳለ ካመነ፣ OHREP ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌርፋክስ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት ጉዳዩን ያሳውቃል።

አንድ አቤቱታ አቅራቢ በፌደራል ትራንዚት አስተዳደር (Federal Transit Administration) ያለበትን አቤቱታውን በቀጥታ ወደሚከተለው ፋይል ማስገባት ይችላል፥ Office of Civil Rights, Attention: Title VI Program Coordinator, East Building, 5th Floor-TCR, 1200 New Jersey Ave., SE, Washington, DC 20590።

County of Fairfax, Virginia

# መድልዎ እንደደረሰ ክስ ማቅረቢያ የአቤቱታ ቅጽ

ፌርፋክስ ካውንቲ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች፣ እንቅስቃሴዎቹ ወይም በሚሰጣቸው ጥቅማጥቅሞች ላይ በፌደራል፣ በስቴት እና በአካባቢ ሕግ ወይም ፖሊሲ የተከለከለ መድልዎ እንደተፈጸመባቸው ክስ ለሚያቀርቡ ግለሰቦች ሁለት ዓይነት የአቤቱታ አቅራረብ መንገዶች አሉት። ይህ የአቤቱታ ቅጽ በዕድሜ፣ በጾታ፣ በጾታዊ ትንኮሳ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በእምነት፣ የቀድሞ ብሔራዊ ማንነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቆዳ ቀለም፣ የፖለቲካ ዝንባሌ ወይም በዕድሜ አንጋፋነት ሁኔታ የተነሳ ለሚደርሱ በደሎች አቤቱታ ለማቅረብ ጥቅም ላይ መዋል ያለበት ቅጽ ነው።

በአካል ጉዳት ምክንያት ለደረሰ መድሎ አቤቱታ ማቅረብ የሚፈልግ ግለሰብ በአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካኖች ሕግ መሰረት በፌርፋክስ ካውንቲ መንግስት የአቤቱታ አቀራረብ ሂደት መሰረት አቤቱታውን ለማቅረብ ለዚሁ የተዘጋጀውን አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ መጠቀም አለበት። የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጹን ቅጂ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ፕሮግራም ቢሮ (Office of Human Rights and Equity Programs) ሠራተኞችን በማነጋገር ማግኘት ይችላሉ።

የፌርፋክስ ካውንቲ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ፕሮግራም ቢሮን ለማነጋገር በስልክ ቁጥር 703-324-2953፣ TTY 711 በማናቸውም የፌርፋክስ ካውንቲ የሥራ ቀናት ከጠዋቱ 8:00  እስከ ከሰዓት 4:30 መደወል ወይም ኢሜይል በ EPDEmailComplaints@FairfaxCounty.gov አድራሻ መላክ ይችላሉ።

***መመሪያ፦*** አቤቱታዎች የተባለው የመድልዎ በደል ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉ 60 የሥራ ቀናት (ከትራንዚት ጋር ለተያያዙ አቤቱታዎች በ180 የቀን መቁጠሪያ ቀናት) ውስጥ ፋይል ሊከፈትላቸው ይገባል። «የሥራ ቀን» የሚለው ቃል ማለት ከሰኞ እስከ ዓርብ ያለ የካውንቲ ክብረበዓል ያልሆነ ቀን ማለት ነው። አቤቱታ ፋይሉ ከተከፈተ በኋላ ምርመራ ይጀመራል።

ይህ ቅጽ በካውንቲው ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ በፌርፋክስ ካውንቲ ፖሊሲ እና አሰራር መሰረት የመድልዎ ክስ በሚያቀርቡ ግለሰቦች ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

**አቤቱታ የሚያስገባው ግለሰብ**

**ስም፦**

**ስልክ ቁጥር፦**

**የቤት፥**
**የመሥሪያ ቤት፥**
**ሞባይል ስልክ፥**
**መደወያ የተሻለ ሰዓት፥**

**ኢሜይል፦**

**አድራሻ፦**

**ጎዳና፥**

**ከተማ፥** **ስቴት፥** **ዚፕ ኮድ፥**

**መድልዎ የፈጸመው ግለሰብ ወይም ዲፓርትመንት፦**

**ስም፥** **ዲፓርትመንት፥**

**ጎዳና፥**

**ከተማ፥** **ስቴት፥** **ዚፕ ኮድ፥**

**ስልክ ቁጥር፥**

መድልዎ የተፈጸመበት ምክንያት(ቶች) (ተገቢነት ያላቸው ላይ ምልክት ያድርጉ)፦

| | | |
|---|---|---|
| ☐ ዘር ______________ | የዕድሜ አንጋፋነት ሁኔታ | የፖለቲካ ዝንባሌ |
| ☐ ቀለም ________ _____ | በቀል | ዕድሜ – የትውልድ ቀን: _______ |
| ☐ የቀድሞ ብሔራዊ ማንነት ________ | ጾታ ወይም ጾታዊ አቋም | ሌላ፦ _ ____________ |
| ☐ ሃይማኖት ____________ | ጾታዊ ትንኮሳ | ሌላ፦ _____________ |
| እምነት _______________ | ☐ የጋብቻ ሁኔታ | ሌላ፦ _____________ |

መድልዎ የደረሰበት ቀን፦ ____________________________________________________________

የአቤቱታ አጭር ማጠቃለያ፦ (አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ገጾችን በዓባሪነት ያያይዙ)

____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________

እንዲወሰድ የተፈለገው እርምጃ፦

____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________
____________________________________________________________________________________

ከዚህ በላይ ያለውን አቤቱታ እንዳነበብኩ እና እኔ እስከማውቀው፣ እስካለኝ መረጃ ወይም እስከማምነው ድረስ እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

____________________________________ ___/___/___

የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማ ቀን

**ይህ ቅጽ ጥያቄው ሲቀርብ በአማራጭ ሌሎች ቅርጸቶች ማግኘት ይቻላል። ጥያቄዎን ወደ Equity Programs Division of the Office of Human Rights and Equity Programs, 12000 Government Center Parkway, Suite 318, Fairfax, VA 22035 ይላኩ ወይም በስልክ ቁጥር 703-324-2953፣ TTY 711 ይደውሉል ወይም በቁጥር 703-324-3305 (ፋክስ) ይላኩ።**